ጥምቀት፤ በአብ በወልድና በመንፈስ ቅዱስ ስም።

በማን ስም ታጠምቃላችሁ ወይም ትጠመቃላችሁ ብሎን የሚጠይቀን ሰው ቢኖር፥ በአብ በወልድና በመንፈስ ቅዱስ ስም እናጠምቃለን፥ እንጠመቃለንም ብለን እንመልሳለን።

ከላይ እንዳየነው አብ ወልድና መንፈስ ቅዱስ፥ አንድ እግዚአብሔር፥ አንድ መለኮት እንጂ ሦስት እግዚአብሔሮች ወይም ሦስት መለኮቶች አይደሉም። ስለዚህ እኛ በአንዱ እግዚአብሔር ማለት በአንዱ አምላክ ስም እናጠምቃለን እንጂ በሦስቱ እግዚአብሔሮች ስም አናጠምቅም።

በአንዱ አምላክ በአብ በወልድና በመንፈስ ቅዱስ ስም የምናጠምቅበትና የምንጠመቅበት ምክንያት ሕይወቱን ለሰው ልጆች አሳልፎ ሰጥቶ ሞትን አሸንፎ የተነሣው ጌታ ኢየሱስ ክርስቶስ ስላዘዘን ነው። ወንጌላዊው ማቴዎስ የጌታን ቃል ሲጽፍ «... ሥልጣን ሁሉ በሰማይና በምድር ተሰጠኝ። እንግዲህ ሂዱና አሕዛብን ሁሉ በአብ በወልድና በመንፈስ ቅዱስ ስም እያጠመቃችኋቸው ያዘዝኋችሁንም ሁሉ እንዲጠብቁ እያስተማራችኋቸው ደቀመዛሙርት አድርጓቸው እነሆም እኔ እስከ ዓለም ፍጻሜ ድረስ ሁልጊዜ ከእናንተ ጋር ነኝ» ይላል። ማቴ. 28፥19-20። እንግዲ ለመሆኑ ከሞት ከተነሣው ከጌታችን ቃል ለኛ የሚበልጥ አለ?

ጌታችን ድል ካደረገ በኋላ በዚህ ሥፍራ ሰግደንና ምድርን ሁሉ ጠቅሶ፣ ሥልጣኑ የማይደርስበት ቦታ እንደሌለ ገልጾ፣ «አሕዛብን ሁሉ» በሚለው ቃሉ ደግሞ የምድርን ሕዝብ ሁሉ አካትቶ፣ «እስከ ዓለም ፍጻሜ ድረስ ሁልጊዜ ከእናንተ ጋር ነኝ» በሚለው ቃሉ ደግሞ እስከ ዓለም ፍጻሜ የሚጸና መሆኑን በማስረዳት ነበር የጥምቀት ትእዛዙን የሰጠው። ከዚህ ቃልና አነጋገር በጌታችን ትእዛዝ መሠረት በአንዱ አምላክ በአብ በወልድና በመንፈስ ቅዱስ ስም ማጥመቅ በቦታ ሳይወሰን፣ እስከ ዓለም ፍጻሜ ድረስ ጌታን አምነው ደቀ መዛሙሩ በሚሆኑ ሁሉ ላይ እንደሚፈጸም ገልጽ ሆኖ ይታያል። ስለዚህ ጌታ እንዳዘዘው በአብ በወልድና በመንፈስ ቅዱስ ስም ማጥመቅ በተወሰነ ጊዜና ቦታ ተደርጎ የቀረ ሳይሆን ከሐዋርያት ጊዜ ጀምሮ ወደ ጌታ በሚመለሱ አሕዛብ ላይ የተደረገ አሁንም እየተደረገ ያለ ወደፊትም የሚደረግ ነው።

ከዚሁ ጋር መታሰብ ያለባቸው ሉቃስ በሐዋርያት ሥራ 2፥38፤ 10፥48፤ 19፥5 «በኢየሱስ ስም» ስለመጠመቅና የኃጢአት ይቅርታን ስለማግኘት የጻፋቸው ጥቅሶች ናቸው። ቤተ ክርስቲያን ይህ የሉቃስ አገላለጽ ሳለ በዘመናት ሁሉና በየአገሩ በአብ በወልድና በመንፈስ ቅዱስ ስም ስታጠምቅ የቆየችውና አሁንም የምታጠምቀው በሁለት ዋና ምክንያቶች ነው።

አንደኛ፡- ቤተ ክርስቲያን በዘመናት የጌታን ቃል ሁሉ ብታከብርም የወንጌሉን ቃል በተለይ ስታከብር ቆይታለች። በዚህ ምክንያት በአንዳንድ አብያተ ክርስቲያናት እስካሁን ድረስ ከአራቱ ወንጌላት ሲነበብ ምእመናን ቆመው ሲያዳምጡ ይታያሉ። ይኸንንም የሚያደርጉት ወንጌሉ የጌታ የኢየሱስ ክርስቶስን ሕይወትና ቃል በቀጥታ ስላሰፈረ ለአክብሮት ብለው ነው። ከሐዋርያ ወይም ከሐዋርያት ተከታይ ይልቅ ከምት

ለተነሣው ጌታቸው ትእዛዝ የበለጠ አክብሮት በመስጠት ጌታ በማቴዎስ ወንጌል 28 ባዘዘው መሠረት ምዕመናን «በአብ በወልድና በመንፈስ ቅዱስ ስም» ሲያጠምቁ ቆይተዋል።

ሁለተኛ፦ ከዚህ በበለጠ ግን ቤተ ክርስቲያን «በአብ በወልድና በመንፈስ ቅዱስ ስም» ስታጠምቅ የቆየችበት ምክንያት በአብ በወልድና በመንፈስ ቅዱስ ስም ማጥመቅ የሐዋርያት ተከታይ የሆነው ሉቃስ በሐዋርያት ሥራ የመዘገበውን «በኢየሱስ ስም ማጥመቅ»ን የሚሸፍንና የሚያጠቃልል እንጂ የሚቃረን ሆኖ ስላላገኘች ነው። አንድ ሰው «በአብ በወልድና በመንፈስ ቅዱስ ስም» ሲጠመቅ በጌታ በኢየሱስ ስምም ተጠምቋል! ምክንያቱም «ወልድ» ማለት ጌታ ኢየሱስ ክርስቶስ ማለት ነውና። ወልድ «ልጅ» ማለት ጌታ ኢየሱስ ክርስቶስ መሆኑን አዲስ ኪዳናችን በብዙ ሥፍራ ይገልጻል። ለምሳሌ ያክል ሮሜ 1፥3-4 ተመልከት። በ1ዮሐ. 5፥12 «ልጁ ያለው ሕይወት አለው የእግዚአብሔር ልጅ የሌለው ሕይወት የለውም» ይላል። በ1ዮሐ. 3፥8 «ስለዚህ የዲያብሎስን ሥራ እንዲያፈርስ የእግዚአብሔር ልጅ ተገለጠ» ይላል። «ልጅ»ን ግዕዙ «ወልድ» ይለዋል። እነሆ በዚህ ሥፍራ «ልጅ» ሲል ሕይወት ስለሆነው ስለጌታ ኢየሱስ እንጂ ስለሌላ ሰው ወይም አምላክ አልተናገረም። ስለዚህ ወልድ ማለት ጌታ ኢየሱስ ክርስቶስ ስለሆነ በአብ በወልድና በመንፈስ ቅዱስ ስም የተጠመቀውን ሰው «በኢየሱስ ስም» እንዳልተጠመቀ መመልከት ስሕተት ነው።

በሌላ በኩል ደግሞ «በኢየሱስ ስም» ብቻ እንጂ በአብ በወልድና በመንፈስ ቅዱስ ስም መጠመቅ አያስፈልግም እንዳንል ከሞት የተነሣው ጌታ ኢየሱስ ራሱ አሕዛብን ሁሉ «በአብ በወልድና በመንፈስ ቅዱስ ስም እያጠመቃችኋቸው ደቀመዛሙርቴ አድርጓቸው...

እኔ እስከ ዓለም መጨረሻ ድረስ ሁልጊዜ ከእናንተ ጋር እሆናለሁ» በማለት ከላይ እንዳየነው በቦታና በጊዜ የማይወሰን የተምቀት ሥርዓት ሰጥቶናል።

ከዚህም ሌላ ከአብ ከወልድና ከመንፈስ ቅዱስ ስም፡- አንዱ የበላይ ነው፥ አንደኛው ደግሞ የበታች ነው፥ እንዳንል ሦስቱም ስም በአንድነትና በእኩልነት ተቀምጠው እናገኛለን። ስለዚህ እኛ የአብን ስም፥ ከወልድና ከመንፈስ ቅዱስ ስም ሳናጋጭ፥ በችሎትና ሥልጣንም ሳናለያይ፥ በአብ፥ በወልድና በመንፈስ ቅዱስ ስም እናጠምቃለን።

የኢየሱስ ስም ብቻ።

ቀደም ብለን እንዳየነው፥ አንዳንድ ወገኖች ጌታችን ኢየሱስ ክርስቶስ በማቴ. 28 የሰጠው የተምቀት ትእዛዝ በቦታና በጊዜ የማይወሰን መሆኑን በመዘንጋት፥ እንደዚሁም ጌታ የሰጠው የተምቀት ሥርዓት በሐዋርያት ሥራና በሌሎች መፍራዎች የተጠቀሰውን የሚያጠቃልል ሙሉ ሥርዓት መሆኑን በመዘንጋት ተምቀታችንን ሐዋርያት በፈጸሙት መልክ «በኢየሱስ ስም ብቻ» ማድረግ አለብን ይላሉ።

እነዚህ ሰዎች የማቴዎስን ሐዋርያነት ረሱ ? ከዚህም ሌላ አሕዛብን ሁሉ በአብ በወልድና በመንፈስ ቅዱስ ስም አጥምቁ እኔ እስከ ዓለም ፍጻሜ ከእናንተ ጋር እሆናለሁ የሚለውን በጊዜና በቦታ የማይወሰነውን የጌታን ቃል የት አደረሱት እንላለን።

ከዚህም በላይ መንፈስ ቅዱስ ከእግዚአብሔር አብ የሚወጣ የክርስቶስ መንፈስ መሆኑን መዘንጋት የለብንም። መጽሐፍ ቅዱስ በብዙ ሥፍራ በመንፈስ ቅዱስ ስለመጠመቅ ይናገራል። ማቴ. 3፥11። በመንፈስ ቅዱስ መጠመቅ ትርጉሙ ምን እንደሆነ ለማተት ይህ ቦታውና ዓላማችን ባይሆንም በአጠቃላይ የእግዚአብሔር አብና

የክርስቶስ መንፈስ በሆነው በእውነት መንፈስ ማለት በመንፈስ ቅዱስ ስም መጠመቅ የጌታ የራሱ ትእዛዝ መሆኑን መዘንጋት የለብንም።

እኛ በመንፈስ ቅዱስ፣ በእግዚአብሔር አብና በጌታ ኢየሱስ መካከል፤ የዓላማ፣ የኅብረት፣ የባሕርይ፣ የህልውናና፣ የመለኮት ተቃራኒነትን አናይም። የሰው ልጅ የደኅንነት ሥራ የተፈጸመው በአብ በወልድና በመንፈስ ቅዱስ ነው። እግዚአብሔር አብ አንድያ ልጁን እስኪልክ ድረስ ዓለሙን እንዲሁ ወደደ። ወልድ ደግሞ ፈቅዶ፣ ራሱን ዝቅ አድርጎ የሰውን ሥጋ በመልበስ ራሱን ስለ ሰው አሳልፎ ሰጠ። መንፈስ ቅዱስ ደግሞ በምእመናን ልብ ውስጥ የኢየሱስ ክርስቶስን ሥራ እውነተኛነትንና ፍጹምነትን እየመሰከረ ሥራውን ተጨባጭ አደረገ። በዚህ ምክንያት እኛ አንዱን ያለሌላው፣ ነጥለን አናመልክም፤ የምናመልከው ግን በአብ በወልድና በመንፈስ ቅዱስ ሦስት አካላት የተገለጸውን አንዱን አምላክ ነው። ስለዚህ ጥምቀታችን አብን ወልድንና መንፈስ ቅዱስን በመነጣጠል፣ ወይም በኢየሱስ ስም መጠመቅ ያድናል የአብና የመንፈስ ቅዱስ ስም ከተጨመረ አያድንም በሚል መንፈስ አይደለም።

የእግዚአብሔር ቃል «የጸጋም ስጦታ ልዩ ልዩ ነው፣ መንፈስ ግን አንድ ነው፣ አገልግሎትም ልዩ ልዩ ነው ጌታም አንድ ነው፣ አሠራርም ልዩ ልዩ ነው ሁሉን በሁሉ የሚያደርግ እግዚአብሔር ግን አንድ ነው» ስለሚል 1 ቆሮንቶስ 12፣4-6፤ «በኢየሱስ ስም ብቻ» እናጠምቃለን የሚሉ ወገኖች፣ ጌታ በማቴ. 28 የተናገረውን፣ ቦታና ጊዜ የማይወስነውን ትእዛዝ በመዘንጋት «በኢየሱስ ስም» ወይም «በክርስቶስ ስም» የሚሉትን ክፍሎች ምርጫቸው በማድረግ ያጠምቃሉ ብለን ልንታገሣቸው በቻልን ነበር። በአጭሩ የጌታ ቃል አሠራርም ልዩ ልዩ ነው ስለሚል ሉቃስ በጻፈው መልኩ

«በኢየሱስ ስም» ለምን ያጠምቃሉ ብለን ባልጠላናቸውና ባልተቃወምናቸው ነበር።

እነዚህ ሰዎች ግን የቃሉን አንዱን ገጽታ ብቻ በመመልከት በኢየሱስ ስም ማጥመቅ አልበቃ ብሎአቸው የሞትና የሲኦል ቁልፍ በእጃቸው ያለ ይመስል በቦታና በጊዜ በማይወሰነው በጌታ በራሱ ትእዛዝ መሠረት በአብ በወልድና በመንፈስ ቅዱስ ስም ተጠምቀው በጌታ የሚያምኑትን ምእመናን አልዳናችሁም እስከ ማለት ይደርሳሉ። በአብ በወልድና በመንፈስ ቅዱስ ስም ተጠምቆ የጌታ ደቀመዝሙርና ምእመን መሆን ወደ ደኅንነት የማያደርስ ከሆነ የተሳሳተው እስከ ዓለም ፍጻሜ ከእናንተ ጋር እሆናለሁ አሕዛብን ሁሉ በአብ በወልድና በመንፈስ ቅዱስ ስም እያጠመቃችኋቸው ደቀመዛሙርት አድርጉአቸው ብሎ ያዘዘው ጌታ ራሱ መሆኑ ነዋ! እኛ ግን ጌታችንም ሆነ ሉቃስ ሁለቱም ትክክለኞች ናቸው እንላለን። ልዩነት ቢኖር የጌታ ቃል የሉቃስን ሐሳብ የሚያጠቃልል ሙሉ ትእዛዝ ሆኖ መገኘቱ ነው።

በበኩላችን እነዚህ ሰዎች አካላትን ሳያደባልቁ «በኢየሱስ ስም» ተጠምቀው፥ እግዚአብሔር በልጁ በኩል ባደረገላቸው ምሕረት ተደስተው ቢኖሩ መልካም ነበር እንላለን። ይህ የእግዚአብሔር ምሕረትና ቸርነት አልበቃ ብሎአቸው «በኢየሱስ ስም» በመጠመቃቸው ይመጻደቃሉ። እግዚአብሔር ሆይ «እኛ በኢየሱስ ስም» የተጠመቅን በትክክለኛው ስምና ፎርሙላ ስለተጠመቅን ድነናል። እነዚያ በአብ በወልድና በመንፈስ ቅዱስ ስም የተጠመቁት ሁሉ ጠፍተዋል ብለው በእግዚአብሔር ዘንድ ተወዳጅነትን ለማትረፍ ከመፈለጋቸው በፊት ያንንስ የተናገረው ማን ነው? ከሞት የተነሣው ኢየሱስ አይደለምን? ብለው ማሰብና መጠየቅ ነበረባቸው። ምሕረትን እንጂ መሥዋዕትን አልወድም የሚለውን ቃሉን ቢያውቁ ኖሮ፥ በየቦታው በዚህ ዓይነት

ካልተጠመቃችሁ ልትድኑ አትችሉም እያሉ የሕግ ሰባኪዎች ባልሆኑም ነበር።

ቀደም ብለን እንደገለጽነው በአጉል ተመጻዳቂነት ለራሳቸው ተሳስተው ደካሞችን ያሳስቱ እንጂ እኛስ በጌታችን በኢየሱስ ክርስቶስ ስም ተጠምቀናል። ምክንያቱም በአብ በወልድና በመንፈስ ቅዱስ ስም ስንጠመቅ የእግዚአብሔር ልጅ /ወልድ/ ብለን የምንጠራው እርሱን ራሱን ኢየሱስን ነውና። ለጌታችን ኢየሱስ ክርስቶስ ስም የሚቀኑና የሚወዱት እነርሱ ራሳቸው ብቻ እንደሆኑ አስመስለው ይናገሩ እንጂ እኛም እንወደዋለን። እርሱ ሕይወት መንገድና እውነት እንደሆነ እንገነዘባለን። ያለእርሱ ሞትና ትንሣኤ ተስፋ እንደሌለን፥ ተስፋችን እርሱ ብቻ እንደሆነ እናምናለን፥ እንገነዘባለን። ሕይወቱን ለእኛ አሳልፎ እንደሰጠ እናውቃለን እናምናለን።

እረ ለመሆኑ በሁለት ሺህ ዓመታት ያህል ውስጥ ሰዎች በሥላሴ ስም ሲጠመቁ ቤተ ክርስቲያን አልነበረችም፥ መንፈስ ቅዱስ አልተሰጠም ማለት ነውን? ይህንን ማሰብ እግዚአብሔር ለብዙ ዘመን ሥራውን አልሠራም ማለት ይሆናል። ይህ ታላቅ ድፍረት ነው።

ስሙን በአግባብና በማስተዋል መጠቀም አለብን።

ኢየሱስ ማን እንደሆነ፥ ያደረገው ሥራ ምን እንደሆነ አስተውለው ሳይረዱት ስሙን ብቻ በድግግሞሽ ቢጠሩት ወይም በምትሐት እንደሚሠራ ዓይነት ቢጠቀሙበት ረብ የለውም። በኢየሱስ ስም ብቻ መጠመቅ አለብን የሚሉ ወገኖች የግድ «ኢየሱስ» የተባለው ስም በጥምቀታችን ካልተጠራ መዳን አይቻልም ብለው ይናገራሉ። እኛ ግን የኢየሱስ ስም በማስተዋልና በእምነት እንጂ እንደ ድግምትና እንደ ምትሐት የግድ መጠራት ያለበት ስም

እንደሆነ አናምንም፤ አንቀበልም። ማስተዋልና እምነት ሳይኖር «የኢየሱስ ስም» ቢጠሩትም አይሠራም። ለዚሁ በሐዋርያት ሥራ 19፥13-16 በአስቄዋ ልጆች ላይ የደረሰባቸው ዓይነተኛ ማስረጃ ይሆነናል።

ሉቃስ በሐዋ. 19፥13-16 የሚከተለውን ጽፎ ይገኛል። «አጋንንት እያወጡ ይዞሩ ከነበሩት አይሁድ አንዳንዶች፦ ጳውሎስ በሚሰብከው በኢየሱስ እናምላችኋለን እያሉ ክፉዎች መናፍስት ባሉባቸው ላይ የጌታን የኢየሱስን ስም ይጠሩባቸው ዘንድ ሞከሩ። የካህናት አለቃ የሆነ አስቄዋ ለሚሉት ለአንድ አይሁዳዊ ይህን ያደረጉ ሰባት ልጆች ነበሩት። ክፉው መንፈስ ግን መልሶ፦ ኢየሱስንስ አውቀዋለሁ ጳውሎስንም አውቀዋለሁ እናንተሳ እነማን ናችሁ? አላቸው። ክፉው መንፈስም ያለበት ሰው ዘለለባቸው ቈስለውም ከዚያ ቤት ዕራቊታቸውን እስኪሸሹ ድረስ በረታባቸው አሸነፋቸውም» ይላል። እነሆ በዚህ ሥፍራ የተጠቀሱ ሰዎች «የኢየሱስን ስም» በመጥራት አጋንንትን ለማስወጣት ይሞክሩ ነበር። ነገር ግን ኢየሱስ ማን እንደሆነ ስላላስተዋሉና አምነውበት ደኅንነት ስላላገኙ ስሙን መጥራታቸው ብቻ ምንም ሊረዳቸው አልቻለም። ዛሬም ቢሆን ኢየሱስ ማን እንደሆነ አስተውለው፥ የሕይወት ጌታና ራስ ካላደረጉት በስተቀር ስሙን እንደምትሐት ሺህ ጊዜ ቢደጋግሙትም አያድንም።

በሌላ አንጻር ስንመለከት ጌታ ኢየሱስ ራሱ ማንነቱን አውቀው በተረዱት በማንኛውም ዓይነት ስም የሚጠሩትንና ክብርን የሚሰጡትን አላውቃችሁም አላድናችሁም ሲል አናየውም። በማቴ. 15፥22 እንደምናየው ከነናዊቷ ሴት «ጌታ ሆይ የዳዊት ልጅ፥ ማረኝ...» ብላ ጮኸች። በጌታ ላይ የነበራት እምነት ታላቅ ስለነበረ ለምን በዚህ ስም ጠራሽኝ ብሎ ሳይፈውሳት አልለቀቃትም። አንደኛው ደግሞ «ጌታ

ሆይ፥ ልጄን ማርልኝ» ብሎ ሲለምነው እናያለን ማቴ. 17፥15። ሌላው ደግሞ «መምህር ሆይ» ብሎ ይጠራዋል ማቴ. 19፥16። ጌታ ኢየሱስ ደቀመዛሙርቱን «ሰዎች የሰው ልጅ ማን እንደሆነ ይሉታል?» ብሎ ከጠየቀና መልሳቸውን ከሰማ በኋላ እናንተስ እኔን ማን እንደሆንሁ ትላላችሁ? ብሎ ጠይቋቸው ነበር። ስምዖን ጴጥሮስ የመለሰው መልስ «አንተ ክርስቶስ የሕያው እግዚአብሔር ልጅ ነህ» የሚል ነው። ጌታም «በሰማያት ያለው አባቴ እንጂ ሥጋና ደም ይህን አልገለጠልህምና ብፁዕ ነህ ...» በማለት አመስግነው። እነዚህን ሁሉ ስንመለከት ጌታ፥ «ኢየሱስ» በላችሁ አልጠራችሁኝምና በዚህ ስም ስላልጠራችሁኝ አልሰማችሁም፥ አላድናችሁም ወይም መልሳችሁ ትክክል አይደለም ሲል አናየውም። እንዲያውም «አንተ ክርስቶስ የእግዚአብሔር ልጅ ነህ» ስላለው ጴጥሮስን ሲያመሰግነው እናያለን።

ከስምም ሁሉ በላይ ያለውን ስም ሰጠው።

ሐዋርያው ጳውሎስ በፊል. 2፥9 «በዚህ ምክንያት ደግሞ እግዚአብሔር ያለ ልክ ከፍ ከፍ አደረገው፥ ከስምም ሁሉ በላይ ያለውን ስም ሰጠው...» ሲል ምን ማለቱ ነው?

ጌታ ኢየሱስ ከፍ ከፍ ማለቱ፥ ከስምም ሁሉ በላይ ያለውን ስም ማግኘቱ የሚገባው ነው። ክብሩን ትቶ በፈቃዱ እስከመስቀል ሞት ድረስ ሄዶ ታላቅ ሥራ በመሥራት የሰዎችን ልጆች ስለዋጀ ክብር፥ ምስጋና ስግደትና አምልኮት ይገባዋል። ራሱን በፈቃዱ ዝቅ ባደረገ መጠን እግዚአብሔር ከፍ ከፍ አደረገው።

«ከስምም ሁሉ በላይ ያለውን ስም ሰጠው» ስንል ግን ከማን ስም በላይ የሆነውን ሰጠው ብለን ልንጠይቅ እንችላለን። ከራሱ ከጥቅሱ ብንመለከት እግዚአብሔር፥

ከእግዚአብሔር አብ ስም የሚበልጥ ስም ለኢየሱስ እንዳልሰጠ ልንረዳ እንችላለን። ጌታ ኢየሱስ በሰማይና በምድር፥ ከምድርም በታች ካሉ ፍጥረታት ሁሉ የሚበልጥ ስም ተሰጥቶታል። እርሱ ጌታ ነው። ለእርሱ ፍጥረት ሁሉ ይሰግድለታል ይንበረከክለታል። በዚህ ምክንያት ግን፥ የኢየሱስ ስም ይኸንን ከስም ሁሉ በላይ የሆነውን ከሰጠው፣ ከእግዚአብሔር አብ ስም ይበልጣል ማለት አይደለም። ቀደም ብሎ ሐዋርያው «በእግዚአብሔር መልክ» ይኖር እንደነበረ ተናግሮ ነበርና። ይህን ስንል ግን በመለኮትነቱ በባሕርዩ ከአብ እንደይማለይ እያረጋገጥን ነው።

እግዚአብሔር የሚጠራበት ብዙ ስሞች አሉት። ከብሉይ ኪዳን ብንጀምር፥ የአብርሃም፥ የይስሐቅና የያዕቆብ አምላክ፤ የእስራኤል አምላክና የሠራዊት ጌታ ከሚጠራባቸው ስሞች ጥቂቶቹ ናቸው። በአዲስ ኪዳንም በአብ በወልድና በመንፈስ ቅዱስ ስም ይታወቃል። በተጨማሪም ሐዋርያው ጳውሎስ በብዙ ሥፍራ «ጌታ» እያለ ይጠራል። ክርስቶስ ኢየሱስ እያለም ይጠራል። ከእነዚህ ሁሉ የእግዚአብሔር ስሞች የትኛው ነው የበላይ የትኛው ነው የበታች? እኛ ከእግዚአብሔር ስሞች ውስጥ አንዱን የበላይ አንዱን የበታች አድርገን አንወስድም። የኢየሱስ ስም ከአብ ስም ይበልጣል፥ ከመንፈስ ቅዱስ ስም ይበልጣል ብለን አናስተምርም። አንዱ እግዚአብሔር የሚጠራባቸው ስሞች እርሱን እስከመለከቱ ድረስ እኩል ናቸው።

«መዳንም በሌላ በማንም የለም፤ እንድንበት ዘንድ የሚገባን ለሰዎች የተሰጠ ስም ከሰማይ በታች ሌላ የለምና» የሐዋ. 4፥12 የሚለውንም በዚሁ መንፈስ እንረዳለን። የሰው ልጅ ሥጋዊም ሆነ መንፈሳዊ ደኅንነት የሚያገኘው በጌታ ኢየሱስ ክርስቶስ በማመን መሆኑ ግልጽ ነው። ዮሐንስ በመልእክቱ የዘላለም ሕይወት

እንዳላችሁ ታውቁ ዘንድ በእግዚአብሔር ልጅ ስም ለምታምኑ ይህን ጽፌላችኋለሁ ሲል ይጽፋል። መዳን በእግዚአብሔር ልጅ ስም /በጌታ ኢየሱስ ክርስቶስ ስም/ ነው ስንል እግዚአብሔር አብ በማዳኑ ሥራ እንደሌለ ልንቆጥር አንችልም። ዮሐንስ ስለ እግዚአብሔር አብ ሲናገር «በዚህ የእግዚአብሔር ፍቅር በእኛ ዘንድ ተገለጠ በእርሱ በኩል በሕይወት እንኖር ዘንድ እግዚአብሔር አንድ ልጁን ወደ ዓለም ልኮታልና» ይላል። 1ዮሐ. 4፥9። እግዚአብሔር አብ ልጁን ጌታ ኢየሱስን ባይልከው ኖሮ እንዴት በልጁ ስም ለመዳን በተቻለ ነበር? እንደዚህ ማለት መድኃኒቱን ስጡኝ፥ መድኃኒት ሰጪውን /ሐኪሙን/ ግን አታሳዩኝ እንደማለት ይሆናል። ከጌታም በኋላ ለእርሱ ለመመስከር የመጣው መንፈስ ቅዱስ ነው። በመንፈስ ቅዱስም ካልሆነ በስተቀር ማንም ኃጢአቱን ተገንዝቦ በንስሐ ወደ ጌታ ኢየሱስ መጥቶ የኃጢአትን ሥርየት ሊያገኝ አይችልም። ከዚህ ስናይ ያለመንፈስ ቅዱስም አማካይነት ሰው ሊድን እንደማይችል እንረዳለን። በተጨማሪም «ሰው ከውኃና ከመንፈስ ካልተወለደ በቀር ወደ እግዚአብሔር መንግሥት ሊገባ አይችልም» ተብሏል። ዮሐ. 3፥5። ከዚህ ሁሉ ስናይ የማዳን ሥራ የአንዱ አምላክ የአብ የወልድና የመንፈስ ቅዱስ ሥራ እንደሆነ እንረዳለን። አብ፥ ወልድና መንፈስ ቅዱስ ስንል አንድ አምላክ ሦስት «አካላት» ማለታችን ነው።

በአካላት መካከል ማለት በአብ በወልድና በመንፈስ ቅዱስ መካከል ያለውን ልዩነትና /አንድነት/ ለማያውቁ ከላይ የተዘረዘረው ላይገባቸው ይችላል። እነርሱ በአካላት መካከል ያለውን ልዩነት ሳይሆን አንድነትን ብቻ ያያሉ። ስለዚህ ሁሉ ነገር በአንዱ በኢየሱስ ብቻ ተፈጸመ ይላሉ። እኛ ግን በአብ በወልድና በመንፈስ ቅዱስ መካከል ያለውን አንድነት ብቻ ሳይሆን ልዩነታቸውንም ቃሉ

እንዳስተማረን እናውቃለን። አንድነቱ በመለኮት፤ በባሕርይ፤ በፈቃድ፤ በዓላማ፤ በህልውና ሲሆን ልዩነቱ ደግሞ በ«አካል» ነው። በዚህም ምክንያት ደኅንነት የእግዚአብሔር አብ ወልድና መንፈስ ቅዱስ ሥራ ነው ብለን እናምናለን። ሰውም የሚድነው በእግዚአብሔር አብ፣ ወልድና መንፈስ ቅዱስ አንድ አምላክ በማመን ነው። በክርስቶስ ማለት በኢየሱስ አምናለሁ የሚል ሰው ቢኖር፣ አምና የሚድነው የእግዚአብሔር አብንና የመንፈስ ቅዱስን አካላት በመካድ አይደለም።

ምዕራፍ አራት።

ሥላሴ በቤተ ክርስቲያን ታሪክ።

ቤተ ክርስቲያን ወደ 2ሺህ ዓመታት ያክል በምድር ላይ ስትኖር ስለ አብ ወልድና መንፈስ ቅዱስ ግንኙነት፥ በእግዚአብሔር ቃል መሠረት ሳትመራመር ተቃዋሚዎችና ተከራካሪዎች ተነሥተውባት መልስ ሳትሰጥ አላለፈችም።

እንደ እውነቱ ከሆነ የሥላሴ ትምህርት ተቃውሞ የተጀመረው የጌታችንን የኢየሱስ ክርስቶስን አምላክነት ለመቀበል ባልፈቀዱ አይሁዶች ነው። ይኸም የሆነው ጌታችን በዚህ ምድር በተመላለሰበት ወቅት ነው። ዋና የተሰናከሉበት ጉዳይ ሰው ሆኖ እያለ ራሱን እንዴት አምላክ ያደርጋል? እንዴትስ የእግዚአብሔር ልጅ ነኝ ይላል? የሚል ነበር።

ጌታችን ግን እውነተኛ የባሕርይ አምላክ ስለነበር፥ እግዚአብሔር አምላክ የሚሠራውን ሥራ በፊታቸው በመፈጸም መለኮትነቱን ገለጸላቸው። በሥራ ብቻ ሳያበቃ በቃልም ነገራቸው። በተለይ ለደቀመዛሙርቱ «እኔና አብ አንድ ነን»፤ «እኔን ያየ አብን አይቶአል፤ ...እኔ በአብ እንዳለሁ አብም በእኔ እንዳለ እመኑኝ፤ ባይሆንስ ስለራሱ ስለሥራው እመኑኝ» እያለ ተናገራቸው። ዮሐ. 14፥9-11።

ጌታችን ኢየሱስ ክርስቶስ ምንም አምላክ ቢሆን፥ እግዚአብሔር አስቀድሞ ባቀደው መሠረት መለኮትነቱን ለመቀበል ፈቃደኛ ባልሆኑ ሰዎች እጅ ለሞት አልፎ ተሰጠ። አምላክም ስለነበረ ሞት ይይዘው ዘንድ ስላልቻለ ሞትን አሸንፎ ተነሣ።

እስከዘመናችን ድረስ የጌታችንን የኢየሱስ ክርስቶስን አምላክነት ያልተገነዘቡ አይሁዶች በእስራኤል ምድርና በዓለም አካባቢ ይገኛሉ።

በቤተ ክርስቲያን ታሪክ ስለ ሥላሴ የስሕተት ትምህርት በማስተማር ቤተ ክርስቲያንን በከፍተኛ ደረጃ ያወከ አርዮስ የተባለ የግብፅ ሰው ነው። ሰይጣን ማወክ ባሕርዩ ቢሆንም የሰላም አምላክ እግዚአብሔር እውነቱን በማውጣት እያሸነፈው ተከታዮቹን በእውነተኛው መንገድ ሲመራቸው ይኖራል።

አርዮስ ማነው?

አርዮስ በ310 ዓ.ም የእስክንድርያ ቤተ ክርስቲያን ሽማግሌ ነበረ። የስሕተት ትምህርቱ በይፋ የወጣው የእስክንድርያ ጳጳስ እስክንድርስ (አለስክንድርስ) በ318 ዓ.ም ስለክርስቶስ አምላክነት ያስተማረውን ትምህርት በተቃወመ ጊዜ ነበር። አርዮስ ከዚህ በፊት በአሕዛብ (በግሪክ) ፍልስፍና «እግዚአብሔር አንድ ነው» የሚለውን ሐሳብ ይዞ በመነሣት፥ አንዱ እግዚአብሔር እያለ፥ ክርስቶስ አምላክ ሊሆን አይችልም፤ ከእግዚአብሔር የተለየ፥ የባሕርይ አንድነት የሌለው ነው በማለት አስተማረ። እንደ አርዮስ ትምህርት፤ ክርስቶስ ከእግዚአብሔር የሚያንስ፥ ከሰው ግን የሚበልጥ፥ በሁለቱ መካከል የሚገኝ ነው። ከዚህም በላይ ለአርዮስ፥ ክርስቶስ ከጊዜ በኋላ የተፈጠረ ፍጡር ነው። በዚህ ምክንያት አርዮስ ከዓለም ፍጥረት በፊት ክርስቶስ የነበረውን ዘላለማዊነት ካደ። እግዚአብሔር በዘላለማዊነቱ ሲኖር ሳለ ከጊዜ በኋላ ክርስቶስን ፈጠረ። በፈጠረው ፍጡር በክርስቶስ አማካይነት ደግሞ ሌሎችን ፍጥረታት ፈጠረ በማለት አስተማረ።

ከትምህርቱ የተነሣ የእስክንድርያው ጳጳስ እለእስክንድርስ በ320 ዓ.ም አርዮስን አወገዘ። አርዮስ

ደጋፊዎች ስላገኘ ቤተ ክርስቲያን ለሁለት ተከፍላ ተበጠበጠች። እዚህ ላይ ልብ ልናደርግ የሚገባን፥ እውነተኛም ሆነ ሐሰተኛ ትምህርት የግል ደጋፊዎች እንዳሉት ነው። አንድ ሰው ብዙ ደጋፊዎች ወይም ተከታዮች ስላገኘ ብቻ ትምህርቱ እውነተኛ ነው ማለት አይደለም። በአርዮስ ትምህርት ምክንያት በቤተ ክርስቲያን የሆነውን መከፋፈል ለማስወገድ ንጉሡ ቈስጠንጢኖስ በ324 ዓ.ም ሆስዮስ የተባለውን ልዩ ጳጳስ ወደ እስክንድርያ ላከ። ይህም ሆኖ መለያየቱ ሊቀር አልቻለም።

አርዮሳውያን የተጠቀሟቸው ጥቅሶች።

አርዮሳውያን ትምህርታቸውን ለመደገፍ ከተጠቀሟቸው ጥቅሶች ውስጥ የሚከተሉት ይገኛሉ።

1ቆሮ. 11፥3 «ነገር ግን የወንድ ሁሉ ራስ ክርስቶስ የሴትም ራስ ወንድ የክርስቶስም ራስ እግዚአብሔር እንደሆነ ልታውቁ እወዳለሁ።»

1ቆሮ. 15፥28 «ሁሉ ከተገዛለት በኋላ ግን እግዚአብሔር ሁሉ በሁሉ ይሆን ዘንድ በዚያን ጊዜ ልጁ ራሱ ደግሞ ሁሉን ላስገዛለት ይገዛል»

ቈላ፥ 1፥15 «እርሱም የማይታይ አምላክ ምሳሌ ነው የሚታዩትና የማይታዩትም ዙፋናት ቢሆኑ ወይም ጌትነት ወይም አለቅነት ወይም ሥልጣናት በሰማይና በምድር ያሉት ሁሉ በእርሱ ተፈጥረዋልና ከፍጥረት ሁሉ በፊት በኩር ነው ሁሉ በእርሱና ለእርሱ ተፈጥርአል»

ሐዋርያው ጳውሎስ በፊልጵስዩስ ምዕራፍ ሁለት እንደ ገለጸው ጌታችን የመለኮት ባሕርይ እያለው ክብሩን በገዛ ራሱ ፈቃድ ትቶ፥ ሰዎችን ለማዳን ዝቅ ማለቱን የሚያሳዩትን እነዚህን ጥቅሶች፣ ጌታችን

ከመጀመሪያውም ባሕርየ መለኮት እንደሌለው አድርገው በመተርጐም አርዮሳዊያን ተሳሳቱ።

ከላይ የተጠቀሱትንና የመሳሰሉትን ጥቅሶች ሐዋርያው ጳውሎስ በፊልጵስዩስ ምዕራፍ 2፥6-11 ላይ ከጻፈው ሙሉ ቃል ጋር አነጻጽረን ብንመለከት መልካም ነው።

«እርሱ በእግዚአብሔር መልክ ሲኖር ሳለ ከእግዚአብሔር ጋር መተካከልን መቀማት እንደሚገባ ነገር አልቈጠረውም ነገር ግን የባሪያን መልክ ይዞ በሰውም ምሳሌ ሆኖ ራሱን ባዶ አደረገ፥ በምስሉም እንደ ሰው ተገኝቶ ራሱን አዋረደ፥ ለሞትም ይኸውም የመስቀል ሞት እንኳ የታዘዘ ሆነ። በዚህ ምክንያት ደግሞ እግዚአብሔር ያለ ልክ ከፍ ከፍ አደረገው፥ ከስምም ሁሉ በላይ ያለውን ስም ሰጠው፤ ይህም በሰማይና በምድር ከምድርም በታች ያሉት ሁሉ በኢየሱስ ስም ይንበረከኩ ዘንድ መላስም ሁሉ ለእግዚአብሔር አብ ክብር ኢየሱስ ክርስቶስ ጌታ እንደሆነ ይመሰክር ዘንድ ነው።»

ከዚህ ክፍል ጌታችን ኢየሱስ ክርስቶስ «በእግዚአብሔር መልክ» እንደነበረ ከመገለጹም ሌላ የእግዚአብሔር አብ ፈቃድ ፍጥረታት ሁሉ ለጌታችን ኢየሱስ ክርስቶስ እንዲንበረከኩ ወይም እንዲሰግዱ መሆኑ ተገልጾአል። ለመሆኑ በሰማይና በምድር ያለ ፍጥረት ሁሉ እንዲሰግድለት የታሰበው ይህ ኢየሱስ ማን ነው? እግዚአብሔር ካልሆነ በስተቀር ታላቁ አምላካችን ከጐኑ ሌላ ፍጡር ስግደትና አምልኮ እንዲሰጠው ይፈቅድ ይሆን? «ከእኔ በቀር ሌሎች አማልክት አይሁኑልህ... እኔ እግዚአብሔር አምላክህ ቀናተኛ አምላክ ነኝና» ያለ እርሱ አይደለምን? ዘጸ. 20፥3-6። እንዲህ ከሆነ ጌታችን ኢየሱስ ክርስቶስ በባሕርዩ አምላክና ፈጣሪ መሆኑ ግልጽ ነው። እለዚያ ሐዋርያው

እዚህ እንደሚለው ፍጥረት ሁሉ ለጌታ ኢየሱስ ክርስቶስ ለመንበርከክ ባልተገባ ነበር።

አርዮስና ተከታዮቹ ከሐዋርያት ዘመንና ከጌታችን ከሕይወቱ ዘመን ጀምሮ በሥራና በቃል ሲገለጽና ሲታመንበት የነበረውን የክርስቶስን አምላክነት በመካዳቸው በቤተ ክርስቲያን ክፍፍል ተፈጠረ። ከዚህ ክፍፍልና መበጣበጥ የተነሣ በክርስቶስ እምና በእግዚአብሔር ኃይል ጠላቶቹን ሁሉ ድል ያደረገው የሮማው ቄሣር፥ ታላቁ ቈስጥንጥንስ በራሱ ገንዘብ በየሥፍራው ያሉ ጳጳሳትና የቤተ ክርስቲያን መሪዎች ኒቂያ በተባለው ከተማ ጉባዔ ተቀምጠው በጉዳዩ በእግዚአብሔር ቃል መሠረት ተወያይተው አልባት እንዲያደርጉ ጠራቸው። ይህም የሆነው በ325 ዓ.ም ነው። በዚህ አጠቃላይ በሆነ የመጀመሪያው የቤተ ክርስቲያን ጉባዔ የተገኙ ጳጳሳት ወደ 318 ይደርሱ ነበር።

በጉባዔው መጀመሪያ ላይ አርዮስና ተከታዮቹ የእምነታቸውን መግለጫ አቀረቡ። መግለጫቸው ግን በጉባዔው ዘንድ ተቀባይነትን አላገኘም። ከዚያ በኋላ የቂሣሪያው ጳጳስ የታወቀው የቤተ ክርስቲያን ታሪክ ጸሐፊ አውሰብዮስ በቤተ ክርስቲያኑ ከጥንት ዘመን ጀምሮ በጥምቀት ጊዜና በሌላ ጊዜ የሚገለጸውን የእምነት መግለጫ አቀረበ። ይህ የእምነት መግለጫ ተቀባይነትን አገኘ። ይህ የእምነት መግለጫ አርዮሳዊያን ስለክርስቶስ የነበራቸውን የተሳሳተ ትምህርት የሚቃወም ቢሆንም ጉባዔው የክርስቶስን ማንነት በማያሻማ ሁኔታ ግልጽ ለማድረግ ጥቂት ሐረጎችን በመጨመር ተቀበለው። እነዚህን ሐረጎች የጉባዔው አባላት ለመጨመር የተገደዱት አርዮሳዉያን በእግዚአብሔር ቃል የማይገኙትን ሐረጎችንና ቃላትን በመጠቀምና በተሳሳተ መንገድ በመተርጐም ስለሚያሳስቱ እነርሱም

እምነታቸውን ግልጽ በሆነ መንገድ ለመግለጽ ስለፈለጉ ነው። በ325 ዓ.ም የጸደቀው የኒቂያ ጉባዔ የእምነት መግለጫ ሙሉ ቃል የሚከተለው ነው።

«እኛ ሁሉን በሚችል የሚታየውንና የማይታየውን በፈጠረ አንድ አምላክ በሚሆን በእግዚአብሔር አብ እናምናለን።

ደግሞም የእግዚአብሔር ልጅ በሆነ፥ ከእግዚአብሔር አብ በተወለደ፥ እርሱ ብቻ ከእግዚአብሔር አብ ባሕርይ በተወለደ ከአምላክ በተገኘ አምላክ፤ ከብርሃን በተገኘ ብርሃን፤ ከእውነተኛ አምላክ በተገኘ እውነተኛ አምላክ፥ በተወለደ እንጂ ባልተፈጠረ፤ ከአብ ጋር በባሕርይ አንድ በሆነ፤ በሰማይና በምድር ያሉ ነገሮችን ሁሉ በፈጠረ፥ ለእኛ ለሰዎችና ለደኅንነታችን በወረደ፥ ሥጋ በመሰደ ሰው በሆነ፥ መከራ በተቀበለ፥ በሦስተኛው ቀን ከሞት በተነሣ ወደ ሰማይ ባረገ በሕያዋንና በሙታን ሊፈርድ በሚመለስ በአንዱ ጌታ በኢየሱስ ክርስቶስ እናምናለን። ደግሞም በመንፈስ ቅዱስ እናምናለን።

ይህ በመጀመሪያ በ325 ዓ.ም በተደረገው ጉባዔ የወጣ መግለጫ ሲሆን በ381 ዓ.ም ስለመንፈስ ቅዱስ ተጨማሪ ማብራሪያ ታክሎበት አሁን የምናውቀው የኒቂያ የሃይማኖት መግለጫ ወጣ።

የዚህ የእምነት መግለጫ መንፈስ ከሐዋርያት ጊዜ ጀምሮ በቤተ ክርስቲያን ሲሠራበት የኖረ ቢሆንም «በተወለደ እንጂ ባልተፈጠረ» «ከአብ ጋር በባሕርይ አንድ በሆነ» የሚሉ ሐረጐች የአርዮስን የተሳሳተ ትምህርት ለመቃወምና የጌታችን የኢየሱስ ክርስቶስን አምላክነት ለማረጋገጥ የገቡ ናቸው።

አንዳንዶች እንደሚናገሩትና እንደሚያስተምሩት በ325 ዓ.ም የተደረገው የኒቂያ ጉባዔና የመግለጫቸው ዓላማ በድምፅ ብልጫ ሦስት እግዚአብሔሮች አሉ ብሉ

ለማስተማር ሳይሆን ክርስቶስን ፍጡር ነው በማለት አምላክነቱን የካደውን የአርዮስንና የተከታዮቹን የስሕተት ትምህርት ለመታወም ነው። እነዚህ ሰዎች ራሳቸው ሦስት እግዚአብሔሮች አሉ ብለው ያስተምሩ እንደሆነ ነው እንጂ የኒቂያ ጉባዔና የሃይማኖት መግለጫቸው አያስተምርም።

የቤተ ክርስቲያን አበው ቀደም ብለው ስለ ጌታችን ኢየሱስ ክርስቶስ አምላክነት በተለይ በዮሐንስ ወንጌል የሚገኙትን፤ ዮሐ. 10፥29-30። ዮሐ. 1፥1፤ 3፥14 ዕብ. 1፥3ና የመሳሰሉትን ክፍሎች በመጥቀስ ለአርዮሳዊያን ለማስረዳት ሞክረው ነበር። በእግዚአብሔር ቃል ተመክረው ጌታን ከማዋረድ ለመመለስ እምቢ ባሉ ጊዜ ግን የጉባዔውን አስፈላጊነት አምነው በመቀበል ለመሰብሰብ ቻሉ።

አርዮሳውያን በትምህርታቸው ብዙዎችን ከማሳሳታቸውም ሌላ የጌታን አዳኝነትና አምላክነት አምነው በሚከተሉ አብያተ ክርስቲያናትና መሪዎቻቸው ላይ ከፍተኛ ስደት አስነሥተውባቸዋል። ከአሕዛብና የጌታን አምላክነት ከማይቀበሉ ከአንዳንድ የይሁዲ እምነት ተከታዮች ጋር በመሆን አብያተ ክርስቲያናትን አቃጥለዋል፥ ደናግላን አዋርደዋል፥ ምእመናንን አሠቃይተዋል። በዚህ ቀውጢ ጊዜ በርቱዕ እምነታቸው ለጌታ በመቆም ከአምስት ጊዜ ያላነሰ ከመንበረ ጵጵስናቸው ቢሰደዱም ሳያወላውሉ አርዮሳዊያንን በመጽናት የተቃወሙ ስሙ ጥር አበው ቅዱስ አትናቴዎስ ነበሩ። ጌታችን ኢየሱስ ክርስቶስ «የስንዴ ቅንጣት በምድር ላይ ወድቃ ካልሞተች ብቻዋን ትቀራለች ከሞተች ግን ብዙ ፍሬ ታፈራለች» እንዳለው ቅዱስ አትናቴዎስ ለእውነት ብለው በመከራ አስፈላጊውን ዋጋ እየከፈሉ ከሃምሣ ዓመታት በላይ በመቆማቸው ቤተ ክርስቲያን አሁን ይዛ ለምትገኘው የኒቂያ የእምነት

መገለጫ ባለውለታዎ ናቸው። ቅዱስ አትናቴዎስ ዕድሜ ጠግበው በ77 ዓመታቸው በ373 ዓ.ም ከ47 ዓመት የጵጵስና አገልግሎት በኋላ አረፉ።

አርዮስና ተከታዮቹ ግን ከመንግሥት ባለሥልጣናት ጋር በመመሳጠር ጌታን የሚያመልኩትንና አትናቴዎስን የሚደግፉትን በማባረር አርዮስን የእስክንድርያ ጳጳስ ለማድረግ አቀዱ። አትደው፥ ቀን ቆርጠው የአርዮስን መሾም ሲጠብቁ አርዮስ ከአንጀት መታወክ የተነሣ ሞቶ አደረ።

እንደ አርዮስ ትምህርት ቢሆን ኖር።

እንደ አርዮስ ትምህርት ቢሆን ኖር እውነተኛው አምላክ ሥጋ ለብሶ፥ ሰው ሆኖ፥ ራሱን ለመገለጽ ባልቻለ ነበር። አምላክ ከሰው አእምሮ በላይ በመሆኑ ራሱን በሰው ደረጃ ዝቅ አድርጐ ለመገለጽ አይችልም የሚል ትምህርት ስለ ነበረ የአምላክን ሥጋ መሆን /ዮሐ. 1፥14/ ሊቀበል አልቻለም። ይህ አስተሳሰብ በግሪኮች ፍልስፍና ላይ የተመሠረተ ነበር። ከዚህም በላይ መለኮትን በሙላት ለመገለጽ የሚችል መለኮት ብቻ ስለሆነ እንደ አርዮስ አባባል ክርስቶስ ፍጡር ብቻ ቢሆን ኖር አምላክ ራሱን ለመገለጽ ስለማይችል ልናውቀው ባልቻልን ነበር። በሦስተኛ ደረጃ የአርዮሳውያን ትምህርት እውነት ቢሆን ለመዳን ባልተቻለ ነበር። ምክንያቱም ሰውን ለማዳንና ከእግዚአብሔር ጋር ሊያስታርቀው የሚችል ራሱ ፍጡር የሆነ ሳይሆን እግዚአብሔር ራሱ ነውና። አራተኛ የአርዮስ ትምህርት እውነት ቢሆን ኖር ክርስቶስን የሚያመልኩ ሁሉ ጣዖት አምላኪዎች በሆኑ ነበር። ምክንያቱም ፍጡርን ማምለክ ጣዖትን ማምለክ ነውና። የእግዚአብሔር ቃል ግን ኢየሱስ ጌታ እንደሆነና ጉልበት ሁሉ ለእርሱ መንበርከክ እንደሚገባው ይናገራል። ፊልጵ. 2፥10-11።

ሰባልዮስ።

ሰባልዮስ ከአርዮስ 100 ዓመት ያህል ይቀድማል። ትምህርቱ ግን እንደ አርዮስ የክርስቶስን አምላክነት መካድ ሳይሆን በአብ፣ በወልድና፣ በመንፈስ ቅዱስ መካከል ያለውን የአካል ልዩነት መካድ ነበር። እንደሰባልዮስ ትምህርት በአብ በወልድና በመንፈስ ቅዱስ መካከል ምንም ዓይነት ልዩነት የለም። አብ ወልድና መንፈስ ቅዱስ የአንዱ አምላክ ስሞች ናቸው። እንደ አብ በብሉይ ኪዳን ሕግን ሰጠ፣ እንደ ልጅ ሥጋ ለበሰ፣ እንደመንፈስ ቅዱስ ሐዋርያትን መራቸው። አንድ ሰው የተለያዩ ኃላፊነቶቹን በሚያመለክቱ በተለያዩ ማዕረጎች መጠራት እንደሚችል አንዱ አምላክ ተከታታይና ኃላፊ በሆኑ መንገዶች ራሱን ገለጠ። ሰባልዮስ በአብ፣ በወልድና በመንፈስ ቅዱስ መካከል ያለውን አንድነት በማስተማሩ መልካም አደረገ። በዚህም ምክንያት በኋለኞቹ መምህራን መካከል ወልድ፤ከአብ ያንሳል፣ መንፈስ ቅዱስ ደግሞ ከወልድ ያንሳል የሚለው ትምህርት ሥር ሳይሰድ ቀረ። በሌላው በኩል ግን በእግዚአብሔር ቃል የተቀመጠውን በአብ በወልድና በመንፈስ ቅዱስ መካከል ያለውን የ«አካል» ልዩነት፣ አንተ፣ እርሱ፣ እኔ፣ እያሰኘ አንዱ ሌላውን ለመጥራት ያበቃውን ልዩነት መካዱ ትምህርቱን አንዱን አቅጣጫ ብቻ የተመለከተ በአንድ ጐን ብቻ የተመሠረተ፣ የስሕተት ትምህርት አደረገው። ከዚህ የተነሣ አቡሊደስና ጠርጡሊያኖስ የተባሉ ስመጥር አበው ትምህርቱን ተቃወሙ።